# *አፋኙ የፕሬስ ህግ በአጨብጫቢው ፓርላማ ፀደቀ*

*ከአምስት ዓመት በላይ ሲያከራክና በአብዛኞቹ ሙያተኞች ሕገመንግስቱን የጣሰ መሆኑ ሲገለፅበት የቆየው የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት ህግ ትላንት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ ፀደቀ፡፡*

*አሁን የፀደቀው የፕሬስ ሕግ ከሕገመንግሥቱ ድንጋጌ ውጭ በመሆኑ እንዳይፀድቅ የሃገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ፕሬስ መብት ተከራካሪዎች ሲያሳስቡ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ ረቂቁ እንዳይፀድቅ አብዛኛዎች የተቃዋሚ የፓርላም አባላት አቋም ይዘዋል፡፡*

*መገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት በሚለው አዋጅ ላይ ነጻነት ሚለውን ቃል ሊሰመርበት ይገባል በማለት በአዋጁ ላይ አስተያየታቸውን መስጠት የጀመሩት አቶ ተመስገን ዘውዴ ዜጎች ያለመሸማቀቅ፤ ያለ ስጋት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በህገ መንግስቱ እንቀጽ 29(2) ላይ«ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው» እንደሚል ጠቁመው ይህ መብት ግን በአሁኑ መገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነት ህግ አልተከበረም ብለዋል፡፡*

*አቶ ተመስገን እንደሚሉት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 29(3) የቅድሚያ ምርመራ በማንኛ ውም መልኩ የተከለከለ ቢሆንም የአሁኑ ህግ ለአቃቤ ህግ በሰጠው መብት ግን በሚሰራጩ ዜናዎች ወንጀል ሊፈጸም ይችላል ተብሎ ከታሰበ ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊት ጉዳዩ እንዲቆም ልያስገድድ ይችላል፡፡ ይህ ህግ የቅድሚያ ምርመራን የሚያጠናክር መሆኑን የጠቆሙት አቶ ተመስገን «አዋጁ የዜጎችን መረጃ ማግኘት መብት የሚገድል ነው» በማለት ተቃውመውታል፡፡*

*የኢሬዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ምሁራን ፤የኢትዮጵያ ጋዜጠኞችና የኢትዮጵያ የኮሚዩኒኬሽን ማህበራት ረቂቅ አዋጁን ሲቃወሙት መቆየታቸውን ገልፀው ረቂቅ አዋጁ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ከተመራ በኋላም ከአንድዳንድ የቃላት ለውጦች ውጪ የተስተካከለ ነገር አለመኖሩን ተናግረዋል፡፡*

*መንግስት ሚዲያውን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ፈልጎ እተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ቡልቻ «የአሁኑ አዋጅ በየትም አለም ያልታየና እጅግ የከፋ በመሆኑ በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ፕሬስ ታሪክ ውስጥ የጨለማ ቀን ነው ብዬ አስባለሁ» ብለዋል፡፡*

*ከተቃዋሚዎች ለተነሱት ጥያቄዎችመልስ የሰጡት አቶ አስመላሽ ወ/ስላሴ የሕግና የአስተዳደር ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀመንበር በበኩላቸው ከ 1994 ዓ/ም ጀምሮ በመገናኛ ብዙሃንና መረጃ ነፃነት ረቂቅ አዋጅ ላይ ሰፊ የሆነ አገር አቀፍ የምክክር መድረክ ሲካሄድ መቆየቱን ሁሉም የሚውቀው ሀቅ መሆኑን ጠቁመው አዋጁ ለፓርላም የቀረበው በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ባለሙዎች ወደ ኢትጵያ መጥተው ተደጋጋሚ ውይይትና ምክክር ከተደረገበት በኋላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አያዘውም « ህጉ የዴሞክራሲ ስርአትንና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ወደላቀ ደረጃ የሚያደርስ ነው» በማለት ምክር ቤቱ አዋጁን እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል፡፡ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ በቅርቡ ከኒውስ ዊክ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የሚጸድቅው የፕሬስ ህግ ኢትዮጵያን በፕሬስ ነፃነት መስፈርት በዓለም አሉ ከተባሉ ሃገራት በግንባር ቀደምትነት የሚያሰልፋት ይሆናል ብለው ቃል ገብተው ነበር፡፡*

*በመጨረሻም አወዛጋቢው አዋጅ በ 290 ድጋፍ በ77 ተቃውሞና በ9 ድምጸ ተአቅቦ ፀድቋል፡፡ በትናንትናው ዕለት በፓርላማ በፀደቀው የመገናኛ ብዙሃንና መረጃ ነፃነት ሕግ ላይ የሚወያይ ወርክሾፕ በዛሬው ዕለት በጊዮን ሆቴል ተጠርቷል፡፡ ወርክሾፑን ያዘጋጁት ሆርን ኦፍ አፍሪካ ኢንስቲትዩት የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፤የሳይንስና ባህል ድርጅት፤ በተመድ ሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽን ናቸው፡፡*